በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት

# ዜና ኢጤሥምኢ

በኢጤሥምኢ ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት በየአስራ አምስት ቀኑ ዘወትር ማክሰኞ በኢንስቲትዩቱ ክንውናኖች ላይ በማተኮር የሚታተም

ቅጽ 1 ቁጥር 8
ሚያዝያ 14 ቀን 2002 ዓ.ም

## የኢንስቲትዩቱ የ9 ወር የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ቀረበ

የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ልዩ ልዩ የስራ ክፍሎች በ2002 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት ውስጥ ያከናወኗቸውን የዕቅድ አፈጻጸሞች የሚተነትን ሪፖርተ በፕላን ፣ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ተጠናቅሮ ቀረበ፡፡ ሪፖርቱ እንደሚያመለክተው ኢንስቲትዩቱ ባለፉት የበጀት አመታት የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በማካሄድ ሦስት የትኩረት አቅጣጫዎችን በመለየት ወደስራ ገብቷል፡፡ እነዚህም ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮችን ማከናወን እና አስፈላጊ የሆኑ ከጤና ጋር የተያያዙ የቴክኖሎጂ ሽግግሮችን ማድረግ ፣ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ትንቢያ ፣ ዝግጁነት፣ መከላከልና ቁጥጥር እንዲሁም የክልል ላብራቶሪዎችን አቅም በመገንባት አስተማማኝና

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

በውስጥ ገጾች:-

- የ9 ወር የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ቀረበ
- ስርዓተ ጤና ምርምር የህብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የጤና ስርዓት ነው›
- ጠቅላላ ዕውቀት

## ‹‹ስርዓተ ጤና ምርምር የህብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የጤና ስርዓት ነው››

### ስርዓተ ጤና ምርምር



አቶ አበበ በቀለ
የጤና ስርዓት ምርምር ዳይሬክተሬት

ምርምር በጥቅል ሲታይ ስርዓት ባለው መንገድ መረጃዎችን መሰብሰብ' መፈተሽ' መተንተንና ስልማትና እድገት የሚበጁ ችግር ፈቺ የሆኑ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለውሳኔ ማቅረብ ነው፡፡ በምርምር ሙያ ሳይ የቆዩ ጠበብቶች እንደሚሉት የምርምር ሥራ ፍፁም ጨለማ በሆነ ክፍል ውስጥ ያሉትን ጥቋቁር ድመቶችን አጥርቶ የማየት ያህል ጥረትና ትኩረትን በእጅጉ የሚጠይቅ ሥራ ነው፡፡

ጤና የማንኛውም ልማት መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም የህብረተሰብን ጤና መንከባከብና መጠበቅ በራሱ ልማት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አንድ አገር ለጤና መሻሻልና መጎልበት የሚያደርገው ጥረት መሠረታዊ ዓላማው የህብረተሰቡ ጤና ተጠብቆ በማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴው አምራች ዜጋ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከዳር ለማድረስ

ወደ ገጸ 2 ዞሯል

# ስርዓተ ጤና ምርምር የህብረተሰቡን ......

የዓለም መንግስታት የድርሻቸውን ያሳሰሰ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: ከሚደረጉት የጥረት አቅጣጫዎች መካከል ዋነኛዎቹ ለጤና ዘርፍ ፍትሀዊ የሆነ የግብአት አመዳደብ' መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ማደራጀት' ተመጣጣኝ የሆነ የአገልግሎት ሽፋንና ተደራሽነት እንዲሁም ከመሠረታዊና ዋነኛ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ከፍ ብሎ በተለያዩ ደረጃ ላሉ ሆስፒታሎች ቀልጣፋ የሪፈራል ስርዓት መዘርጋት ናቸው::

የኢትዮጵያ ጤናና ስነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት በጤና ዙሪያ በአገር አቀፍ ደረጃ ጥናትና ምርምር የሚያካሒድ የምርምር ማዕከል ነው:: ኢንስቲትዩቱ በቅርቡ ባካሄደው ስር ነቀል የአሰራር ስርዓት ለውጥ መሠረት ከተሰየሙት ከአሥር የማያንሱ ዳይሬክቶሬቶች መካከል አንዱ የጤና ስርዓት /ሔልዝ ሲስተም/ ምርምር ዳይሬክቶሬት ነው::

የስርዓተ ጤና ምርምር በጤናው ዘርፍ ያሉትን ማህበራዊ ጉዳዮች' የግብአት አጠቃቀም' የጤና አገልግሎት አደረጃጀትና ሥራ ሒደት' ዘመናዊ የጤና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም' የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እንዲሁም ህብረተሰቡ በጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ስመገልገል ያለውን ፍላጎትና ተመሳሳይ ሁኔታዎችን አካትቶ የሚያጠና ነው::

## የስርዓተ ጤና ምርምር ባሕሪያት

ቅድሚያ በሚሰጣቸው የጤና አገልግሎት ችግሮች ላይ ትኩረት መስጠት' ከሚመለከታቸው አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የልማት አጋሮችን በተቀናጀ መልኩ በማሳተፍ ወጪ ቆጣቢ የጥናት ስልቶችን መጠቀም'በዚህ ዘርፍ የጤና አገልግሎት አደረጃጀት' አመራር' አገልግሎት አሰጣጥና ተደራሽነት እንዲሁም የአገልግሎቱን ጥራት የሚያጠና ዘርፍ ነው::

## የመድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች አቅርቦት'

የህብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የጤና ስርዓት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ህሙማንን ፍትሀዊ በሆነ መልኩ መሠረታዊ የሆኑ ደህንነታቸውና ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ መድኃኒቶችን የሚያገኙበትን እንዲሁም ሌሎች የሕክምና መገልገያዎች በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉና የበለጠ የሚሻሻሉበትን ስልት የሚያጠና ነው::

## የጤና ባለሙያዎችን በተመለከተ'

በጤናው ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች በሙሉ አመራሩን ጨምሮ ቀዳሚ ተግባራቸው የወገንን ማለትም ህብረተሰቡን ከበሽታ መከላከልና ጤናው የተጠበቀ አምራች ዜጋ ማፍራት ነው:: በመሆኑም በጤናው ዘርፍ የተነደፉትን የትምህርትና ሥልጠና ይዘት የባለሙያዎችን ቅን አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሀም በመንግሥትና በግል የሕክምና መስጫ ተቋማት የሚደረገውን የጤና ባለሙያዎች ፍልሰት መንስኤውንና መፍትሔውን የሚያጠና ነው::

## የጤና መረጃ ፍሰትን በተመለከተ

የጤና መረጃ ስርዓት መረጃዎቹን በወቅቱ መሰብሰብ' መተንተንና አስችኳይ የመፍትሄ እርምጃዎች በሚመለከታቸው የአመራር አካላት እንዲወሰድ ማድረግ ነው::: ይህ በአግባቡና ቀጣይነት ባለው መልክ መከናወን ያለበት ሲሆን በህብረተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለውን የጤና ቀውስ በአጭር ጊዜና መጠነኛ ወጪ መቅጨት የሚያስችል ነው:: ይህን በተመለተ በጤናው ዘርፍ ያለውን የመረጃ ፍሰት እንዲሁም ስልታዊ የመረጃ አጠቃቀምን አስመልክቶ ጥናት ያካሒዳል::

## የጤና በጀት

ቀልጣፋ የሆነ የጤና ስርዓት የህብረተሰቡ ጤና እንዲጠበቅ ለጤና የሚሆን በጀት የሚጎለብትበትን የተለያዩ ስልቶች ይቀይሳል:: ስለሆነም ህብረተሰቡ የሚያስፈልገውን የጤና አገልግሎት በወቅቱ እንዲያገኝ ያስችለዋል:: በቂ በጀት በሚኖርበት ጊዜ የሕክምና አገልግሎ መስጫ ተቋማት ለህብረተሰቡ ተመጣጣኝ የሆነ የማከም' የመከላከልና የመቆጣጠር አልግሎት እንዲሰጡ ያስችላቸዋል:: በመሆኑም ህብረተሰባችን በባህላዊ ተቋማት እንደ ዕድር' ዕቁብ በመሳሰሉት ያዳበረውን መልካም የመረዳዳት/የመተጋገዝ ተሞክሮ በዘመናዊ የጤና ኢንሹራንስ ሊደራጅ የሚችልበትን መንገድ ያጠናል::

## መልካም አመራርና አስተዳደር

በማንኛውም የልማት ዘርፍ የአመራር ስርዓት የሚጫወተው ሚና አጅግ ወሳኝ ነው:: በመሆኑም ውስን የሆነውን የአገር ሐብት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መጠቀም የሚያስችል አመራር መስጠት የመሳሰሉት ሲሆኑ ቁልፍ የትኩረት አቅጣጫዎቹም ስልታዊ ፓሊሲና የአፈጻጸም መመሪያ' ቅንጅታዊ የአሰራር ስልት መዘርጋትና ተጠያቂነትን ማስፈን ነው:: በዚህ ዙሪያ በጤናው ዘርፍ ስላለው

ወደ ገጸ 3 ዞሯል

## ስርዓተ ጤና ምርምር የህብረተሰቡን ......

የአመራር ሁኔታ ጥናት በማካሔድ መጥፎ አዝማሚያዎች የሚወገዱበትንና መልካም አሰራሮች የበለጠ የሚጠናከሩበትን መንገድ ማጥናት ነው፡፡

ከፍ ብሎ ከተዘረዘሩት የትኩረት አቅጣጫዎች አኳያ የተለያዩ አገራት ለየአገራቸው የሚበጅ የአሰራር ስርዓት ያሰፍናሉ፡፡ ከተለያዩ የአሰራር ስርዓቶች የሚበጀውን ለመምረጥ ደግሞ ጥናት መካሔድ በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ መስጠት ውጤቱን ጠቃሚና የጎላ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ሳለፉት በርካታ ዓመታት በተለያየ ደረጃ ያሉ የጤና አመራር አካላት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነት ከምንጊዜም የላቀ ነው፡፡

በመሆኑም ከላይ በተገለፁት አቅጣጫዎች ዙሪያ የስርዓተ ጤና /ሄልዝ ሲስተም/ ዳይሬክቶሬት ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም በአገር/በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኙ የልማት አጋሮችና ተባባሪዎች ጋር በመሆን ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶችን ያካሂዳል፡፡

**‹‹ጠበብቶች እንደሚሉት የምርምር ሥራ ፍፁም ጨለማ በሆነ ክፍል ውስጥ ያሉትን ጥቋቁር ድመቶችን አጥርቶ የማየት ያህል ጥረትና ትኩረትን በእጅጉ የሚጠይቅ ሥራ ነው››**

# የኢንስቲትዩቱ የ9 ወር ...

ቀጣይነት ያለው የላብራቶሪ ስርዓት መዘርጋት ናቸው፡፡
በሪፖርቱ የጤናውን ዘርፍ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ማዕቀፍ መነሻ በማድረግ የኢንስቲትዩቱ የ5 አመት ስትራቴጂክ እቅድ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡

ሪፖርቱ እንደሚጠቁመው የህብረተሰብ ጤና ስጋቶችን አስቀድሞ የመለየትና የቅድመ ዝግጅት ስራ የተሠራ ስሆን

በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱትን በሽታዎችና የጤና ስጋቶች ላይ ቅኝት በማካሄድ ለሚመለከታቸው አካላት መረጃ የመስጠት ስራ ተከናውኗል፡፡ በ9 ወር ውስጥ ለተከሰቱ ወረርሽኝ በሽታዎች ለምሳሌ አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት እንዲሁም ማጅራት ገትር እና ለሌሎች የጤና አደጋዎች ተገቢው እርምጃ ተወስዷል፡፡ የወረርሽኝ ጥቆማዎችን በማረጋገጥም የቁጥጥር ስራዎች ተሰርቷል፡፡

ከዚህ በሻገር የድንገተኛ አደጋ ማስተባበሪያ ማዕከል (Emergency Operation Center) በኢንስትቲዩቱ ለመመስረት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በዚህ 9 ወር ጊዜ ውስጥ በተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች 26 ፣ በምግብ ሳይንስና ሥነ ምግብ 9፣ እንዲሁም በባህላዊ መድሀኒቶች 8 ችግር ፊቺ ምርምሮች እየተካሄዱ መሆናቸው በሪፖርቱ ተገልጿል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የክልል ላቦራቶሪዎችን አቅም ለመገንባት በጥራት ቁጥጥር ፣ የላብራቶሪ ባለሙያዎችን በማሰልጠን ፣የቁሳቁስና የገንዘብ ድጋፍ እና የላብራቶሪ መሣሪያዎችን ጥገና በማድረግ ተገልጋዩ ኀብረተሰብ ያልተቋረጠ የላብራቶሪ አገልግሎት እንዲያገኝ ጥረት መደረጉን ሪፖርቱ ይጠቁማል፡፡

የዘጠኝ ወር እቅዱ የየሥራ ክፍሎቹን ዕቅድ የተከናወኑ ተግባራትን ፣ያጋጠሙ ችግሮችን ፣የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን፣ የወደፊት አቅጣጫዎቹን እና ስራዎችን ለማከናወን በስራ ላይ የዋለ በጀትን አካቶ ቀርቧል፡፡



# ጠቅላላ ዕውቀት

የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት

## ሄች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የወንዶች ሚና

ሄች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ መተላለፍ ስንል አንድ ሄች አይ ቪ ያለባት እናት ቫይረሱን ወደ ምትወልደው ልጅ በእርግዝና ፣ በምጥ ፣ በወሊድ ወይም ጡት በማጥባት ወቅት ስታሰተላልፍ ነው፡፡፡ ሄች አይ ቪ ያለባቸው እናቶች ቫይረሱ ወደ ህጻኑ እንዳይተላለፍ የሚያስችለውን መድሃኒት እስካልተጠቀሙ ድረስ ከ15-30 በመቶ ከሚጠጉ ሄች አይ ቪ ካለባቸው እናቶች የሚወለዱ ህጻናት በእርግዝናና በወሊድ ወቅት በሄች አይ ቪ ይያዛሉ ፡፡ ከ5-20 በመቶ የሚደርሱ ሌሎች ህጻናት ደግሞ በጡት ወተት አማካኝነት ሄች አይ ቪ ይተላለፍባቸዋል፡፡

### ያለመከላከያ የሄች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ የመተላለፊያ መጠን

በእርግዝና ወቅት ..................ከ5-10በመቶ
በምጥና በወሊድ ወቅት ...........ከ10-15በመቶ
ጡት በማጥባት ወቅት..............ከ5-20 በመቶ
በአጠቃላይ ጡት ባለማጥባት .....ከ15-25በመቶ
በአጠቃላይ እስከ ስድሰት ወር ድረስ ጡት በማጥባት ....20-35በመቶ
በአጠቃላይ ከአስራ ስምንት እስከ ሃያ አራት ወር ድረስ ጡት በማጥባት ....ከ30-45በመቶ

### አባወራ ከእናት ወደ ልጅ ሄች አይ ቪ እንዳይተላለፍ በሚሰጠው አገልግሎቶች ምን ተሳጥፎ ሲያደርግ ይችላል?

- የሄች አይ ቪ ምርመራና የምክር አገልግሎት በማድረግ የቤተሰብ ምጣኔ አማራጭን በመወሰን
- የትዳር አጋሩ የእርግዝና ክትትል እንድታደርግ ድጋፍ በመስጠት
- ከእናት ወደ ልጅ ሄች አይ ቪ እንዳይተላለፍ በሚሰጡት የምክር አገልግሎቶች ተሳታፊ በመሆን
- የትዳር አጋሩ በጤና ባለሙያዎች እንክብካቤ በጤና ድርጅቶች እንድትወልድ በማበረታታትና በማመቻቸትየ ትዳር አጋሩ ሄች አይ ቪ ወደ ህጻኑ እንዳይተላለፍ የሚሰጠውን ፀረ ሄች አይ ቪ መድሃኒት በትክክል እንድትወስድ በመርዳት
- ልጁ ከተወለደ በኃላ እናቲቱ ተገቢው የህፃናት አመጋገብ ሥርዓት እንድትከተል እገዛ በማድረግ
- የትዳር ተጓዳኙ ከወለደች በኃላ የእርሷንና የህፃኑን ጤንነት በመንከባከብ
- የተወለደ ህፃን ሄች አይ ቪ እንዲመረመር በማድረግ
- አስፈላጊ ምግቦችን በመግዛት ጉዳይ
- የትዳር ተጓዳኙ ወደ ክሊኒክ ስትሄድ ምግብ በማቅረብ ፣ መጓጓዣ በማመቻቸት
- ለተጓዳኙ የስነ ልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ በማድረግ ሲያግዝ ይችላል፡፡

### ከእናት ወደ ልጅ ሄች አይ ቪ እንዳይተላለፍ በሚሰጠው አገልግሎት የወንዶች ተሳትፎ ጠቀሚታ አለው

- ሄች አይ ቪ ምርመራ የማድረግ ፍላጎትን ይጨምራል
- ፀረ ሄች አይ ቪ መድሀኒት እንዲጠቀሙ ያበረታታል ፣ያመቻቻል
- ኮንዶምን እንዲጠቀሙ ያስችላል
- የመውለጃ ቦታ ምርጫ ወሳኔን ያግዛል
- በተጓዳኞች መካከል ግልፅ ውይይት እንዲኖር ያደርጋል
- ስሚወለደው ህፃን ልጅ አመጋገብ ምርጫ ድጋፍ ያስገኛል
- የቤተሰብ ምጣኔ ምርጫን ያግዛል፡፡

### ለግንዛቤዎት

ሄች አይ ቪ እንዳለባቸው በምርመራ ያረጋገጡ ሰዎች ሄች አይ ቪ ውጤታቸውን ለማን ፣ ለምንና እንዴት መናገር እንዳለባቸው የመወሰን መብት አላቸው ፡፡
ሄች አይ ቪ ያለባቸው ተጓዳኞች ልጅ ለመውለድና ላለመውለድ የመወሰን መብት አላቸው ፡፡ ለመውለድ የወሰኑ ከሄች አይ ቪ ጋር የሚኖሩ ባልና ሚስት ጤናማ እርግዝናና ከሄች አይ ቪ ነፃ የሆነ ልጅ እንዲኖራቸው ተገቢውን የህክምና እንክብካቤና ማህበራዊ ድጋፍ ማግኘት አለባቸው ፡፡

ባልና ሚስት ሄች አይ ቪ በደማቸው እንዳለ ከታወቀ ከእርግዝና በፊት ለመውለድ ወይም ላለመውለድ መወሰን ይገባቸዋል ፡፡ መውለድ ካልፈለጉ የመረጡትን ዓይነት የእርግዝና መከላከያ መጠቀም ይችላሉ ፡፡ ኮንዶም እርግዝናን ከመከላከሉ ሌላ ተጨማሪ የሄች አይ ቪ ኢንፌክሽን እንዳይከሰት ስለሚከላከል አዘውትሮ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡
መውለድ ከፈለጉ ግን አስቀድመው ከእናት ወደ ልጅ ሄች አይ ቪ እንዳይተላለፍ የሚሰጠውን አገልግሎትና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም እራሳቸውንና የሚወለደውን ልጅ ጤና መጠበቅ አለባቸው ፡፡
ሄች አይ ቪ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ የሚሰጥ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን ወንዶች አምነው መቀበልና ያለውን አማራጭ ለመጠቀም ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡

**ምንጭ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር**

## ዜና ኢጤሥምኢ

በኢትዮጵያ የጤናና ሥነምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ሕዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት በየአስራ አምስት ቀኑ ዘወትር ማክሰኞ የሚታተም

አዘጋጆች፡-
አቤል የሻነህ
ፍቃዱ በሻህ
ፀሐይነሽ ኤልያስ
ዳግም መርሻ

ፎቶግራፈር፡-
ጽግነሽ ፀጋዬ

ጽሑፍ፡-
ክብነሽ እንግዳ

+25112 751522
+25112 753470
+251 1 754744
+251 1 757722
1242/5654
ehnri@telecom.net.et